# የቆዳ ቴክኖሎጂስቶች አዳዲስ ያለቀላቸዉየቆዳ ምርቶችን አለሙ

ከኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲተዩት እና ከጣልያኑ የኬሚካል አምራች ኮዴይኮ የተወጣጡ የቆዳ ቴክኖሎጂስቶች አዳዲስ ያለቀላቸዉየቆዳ ምርቶችን አለሙ፡ ሁለቱ አካላት በሀምሌ 2007 ዓ.ም ቴክኒካዊ ደጋፍ ለማስጠትና የተለያዩ ምርቶችን ለማልማት የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዉወደ ስራ ገብተዋል፡፡

በመግባቢያ ስምምነቱ ማሰረትምሁለቱ አካላት አዳዲስ ለኤክስፖርት ተመራጭያለቀላቸዉየቆዳ ምርቶችን በተለይም ዝቅተኛ ጥራት ያለዉን ጥሬ እቃ በማሻሻል የማልማት ስራን አከናዉነዋል፡፡ እንደ ባለሞያዎቹ የለሙት ምርቶች አዳዲስ ፋሽን የሆኑ ያለቀላቸዉየቆዳ ምርቶች ናቸዉ፡ ባለሞያዎቹ ለተለያዩ የቆዳ ዉጤቶች ምርት የሚዉሉ 24 የሚደረሱ ስብጥር ያላቸዉምርቶችን ማለማታቸዉንም አስታዉቀዋል፡፡



አዳዲስ የለሙትን ምርቶች ለማስተዋወቅ በተዘጋጀ ሞርሃ ግብር ላይ በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የምርትና ምርታማነት ዘርፎች ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ሀላፊ አቶ ብርሃኑ ንጉስ እንዳሉት ፕሮጀክቱ በኢንስቲቱዩቱ ባለሞያዎች ሙሉ ተሳትፎ የተከናወነ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ በእዉቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ ያለሚዉን ግብ ለማሳካትምከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

አቶ ብርሃኑ እንዳሉት ምርትን በስፋት አምርቶ ለገባያ በማቅረብረገድ በኢንስቲትዩቱ የሚከናወን ምንምተግባር ስለሌለ አዳዲስ የተገኙትን እዉቀቶችና ቴክኖሎጂዎች በአፋጣኝ ወደ ኢንዱስትሪዎች ለማስፋፋት ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

ከፕሮጀክቱ የተገኙት ምርቶች ጥሩ እና አርኪናቸዉያሉት አስተባባሪዉከዚህ የምንረዳዉ ኢንስቲትዩቱና የያዛቸዉማሳሪያዎች የተለያዩ ምርምሮችን በቆዳ እና ቆዳ ዉጤቶች ቴክኖሎጂ ዙሪያ ለማስራት ብቁ ሚሆናቸዉን ነዉተናግረዋል፡፡

በፕሮጀክቱ ላይ የተሳተፉ የኢንስቲትዩቱ ባለሞያዎች በበኩላቸዉከጣልያን ከማጡና በቂ ልምድ ካላቸዉ የቆዳ አመራረት ቴክኖሎጂስቶች ጋር በጋራ ማስራታቸዉለነሱ ሜልካምአጋጣሚመሆኑን ተናግረዉ፤ አንድን ፕሮጀክት እንዴት መተግበር እንዳለባቸው፣ ችግሮችን እንዴት መፍታት እንዳለባቸዉና አንድን አዲስ ምርት ከመጀመሪያዉእስከ መጨረሻዉእንዴት አልምተዉእንደሚያዉጡበቂ እዉቀት መቅሰማቸዉን ተናግረዋል፡፡

ባለሞያዎቹ እንደሚሉት ከፕሮጀክቱ ከጥሬ ቆዳ እና ሌጦ ጥራት እንዲሁምከማጠናቀቅ ቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ ከፋብሪካዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች መፍትሄ ለማበጀት የሚያስችል እዉቀት አግኝተዋል፡፡





ፕሮጀክቱ አዳዲስ ምርቶችን አልምቶ ወደ ፋብሪካ የማስተላለፍ የራስ መተማመናችንንምአሳድጎልናል ብለዋል፡፡

በፕሮጀክቱ የተሳተፉ ከጣልያኑ የኬሚካል አምራች ኮዴይኮ የማጡየ ቆዳ ቴክኖሎጂስቶች በበኩላቸዉ የለሙት ምርቶች አዳዲስ የፋሽን አይነቶች መሆናቸዉን ተናግረዋል፡፡ የኢንስቲትዩቱ ባለሞያዎች አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅ ያላቸዉን ተነሳሽነት ያደነቁት ቴክኖሎጂስቶቹ የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች አዳዲስ ምርቶችን በራሳቸዉአቅምየማምረት ብቃት እንዳላቸዉምአረጋግጠዋል፡፡

